
# የቤተሰብ ሐኪም ኣስፈላጊ ነው

**⚠ መጀመርያ ወደ የቤተሰብ ሐኪምዎ ይሂዱ**




የቤተሰብ ሐኪሞች የእርስዎ ዋና የጤና እንክብካቤ ሰጪ ናቸው በጤናዎ እና ደህንነትዎ ላይም ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። እነሱን በየጊዜው ማየት ኣስፈላጊ ነው። የቤተሰብ ሐኪሞች ኣጠቃላይ ሐኪሞች ወይም የመጀመርያ ደረጃ እንክብካቤ ሰጪ ሐኪሞች ተብለውም ይጠራሉ።

---

## የቤተሰብ ሐኪሞች በሚከተሉት መንገዶች የተለመዱ የጤና ችግሮችን በመለየት (በመመርመር) ያክማሉ።

- የሰውነት ክፍልዎን በመመልከት፣ በማዳመጥ፣ እና በመመርመር
- ስለሚከተሉት ነገሮች ጥያቄ ይጠይቅዎታል
  - ስለ ጤናዎ
  - ስለ የቤተሰቦችዎ ጤና
  - ስለ ሂወትዎ እና ስለ የእለት ተእለት ተግባርዎ( ለምሳሌ ኣመጋገብ፣ የሰውነት እንቅስቃሴ፣ ማጨስ፣አልኮል መጠቀም፣  ኣደንዛዥ ዕጽ መጠቀም፣ ስራ እና የኣኗኗር ሁኔታዎች)
- ከሌሎች የጤና ኣገልግሎቶች እና ልዩ ባለሞያዎች ጋር ማገናኘት
- እንክብካቤን መከታተልና ማስተባበር። የምርመራ ውጤቶችን ያብራራሉ።
- ምርመራዎችን ማዘዝ( እንደ የሽንት፣ የደም፣ ወይም የራጂ)

---

**811 Health Link**
Advice 24/7

**ሐኪም ለማግኘት እርዳታ ሲፈልጉ 811 ይደውሉ**
**https://albertafindadoctor.ca/**
የትርጉም ኣገልግሎት ሊኖር ይችላል


BY NC ND


ከህዳር 5፣ May, 2025
ጽሑፍ፥ አልበርታ የካንሰር እንክብካቤ፡ አልበርታ የጤና አገልግሎ


Alberta Health Services